# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት

## አቅራቢዎች

# እግዚአብሔር ባሪያውን ዮሴፍን አክብሮታል




**ጸሐፊው**: Edward Hughes

**የተተረጎመው**: Eyerusalem Dechasa

**ምሣሌ አቅራቢው**: M. Maillot; Lazarus

**ያሻሸለው (አሻሽሎ የጻፈው)**: M. Maillot; Sarah S.


**ታሪክ** 8 **ከ** 60 **ዎቹ መሃከል**


**www.M1914.org**

***Bible for Children,*** *PO Box 3, Winnipeg, MB R3C 2G1 Canada*



ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል
ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።


**አማርኛ** Amharic








የተጨነቁ ሰዎች "ማንም
ሰው ሕልማችን ምን ማለት
እንደሆነ ሊያሳየን አይችልም" ብለው
መለሱ። "እግዚአብሔር ይችላል!" ዮሴፍም
"ሕልማችሁን
ንገሩኝ"
አላቸው።
3


"ሕልምህ በሦስት ቀናት ውስጥ
ወደ ንጉሱ ፈርኦን ዘንድ ትመለሳለህ
ማለት ነው" ብሎ ለእልፍኝ አሽከሩ
ነገረው።
በተፈታህ ጊዜ
"አስታውሰኝ
እናም ፈርዖን
እንዲፈታኝ
ጠይቅልኝ"
አለው።
4


የዳቦ ጋጋሪው ህልም መጥፎ ዜናን
ይዞ ነበር። "በሶስት ቀን ውስጥ
ትሞታለህ" የሚል ነበር። ሁለቱም
ሕልሞች
እውን ሆኑ።
5


ነገር ግን የእልፍኝ አሽከሩ ዮሴፍን ረሳው።
ፈርኦንን አንድ ቀን ከእንቅልፉ ሲነቃ ተረብሾ
ነበር። "ሕልም አይቼ ነበር" እያለ
ጮኸ። ሆኖም ግን ከጠቢባኑ
መካከል
አንዳቸውም
ትርጉሙን
ሊያሳዩት
አልቻሉም።
በድንገት የእልፍኝ አሽከሩ
በእስር ቤት ያለውን ዮሴፍን
አስታወሰው። ለፈርዖንም ስለ
እርሱ ነገረው።
6


ፈርዖንም ወዲያውኑ ወደ ዮሴፍ ላከበት።
"ሕልም ከእግዚአብሔር የመጣ መልእክት ነው"
በማለት ዮሴፍ ለንጉሡ ነገረው። "ግብፅ ሰባት
ዓመታት የተትረፈረፈ እህል, ከዚያም ሰባት
ጥማትና ረሃብ ይኖርባታል." አለው።
7


ዮሴፍም ፈርዖንን "በሚመጡት
በሰባቱ መልካም አመታት እህል
ለማከማቸት እቅድ አውጡ
ይህካልሆነ ግን ህዝቦችህ
እስከሞት ድረስ
ይራባሉ" ሲል
መከረው።
ፈርዖንም
"እግዚአብሔር
ከእናንተ ጋር
ነው ከእኔም
በኋላ በግብፅ
ላይ ትነግሳለህ"
አለው።
8


ሰባቱ የጥጋብ ዓመታት መጡ። ከዚያም በኋላ ሰባት የረሃብ ዓመታት ተከተሉ። በሁሉም ሀገር የምግብ እጥረት ተከሰተ። በግብፅ ግን ብዙ ምርቶችን አከማችተው ስለነበር አልተራቡም። የያዕቆብ ቤተሰቦችም ተርበው ነበር።
9


ከተለያዩ አገሮች የመጡ ሰዎች እህል ለመሸመት ወደ ግብጽ ሄዱ። ያዕቆብም ልጆቹን "እናንተም ለመሸመት መሄድ አለባችሁ ካልሆነ ግን እስክንሞት ድረስ እንራባለን"
ሲል አዘዛቸው።
ግብፅ እንደደረሱም እህል ለመሸመት መዘጋጀት ጀመሩ።
10


የያዕቆብ ልጆች በግብፅ ላይ በተሾመው ጌታ ፊት ለፊት ሰገዱ። እነሱም ወንድማቸውን ዮሴፍን አላውቁም ነበር። ነገር ግን ዮሴፍ አወቃቸው። ዮሴፍም ባያቸው ጊዜ የልጅነት ህልሞቹን አስታወሰ። እግዚአብሔር ከወንድሞቹ በላይ ከፍ አድርጎታልና።
11


ዮሴፍ በጣም ጥበበኛ ስለነበር እንደማያውቃቸው ሆኖ አናገራቸው። "እህሉን ወስዳችሁ ወደ ቤታችሁ ሂዱ።
12


ነገር ግን ስትመለሱ ታናሽ ወንድማችሁን ይዛችሁ ተመለሱ በዚህም ሰላዮች እንዳልሆናችሁ አረጋግጣለሁ"
ብሎ አዘዛቸው።
13


ለዚህም ደግሞ ወንድማቸውን ስምኦንን በመያዝ እሱ ጋር አስቀረው። ወንድሞቹም ከብዙ አመታት በፊት ዮሴፍን እንደባሪያ በመሸጣችን እግዚአብሔር እየቀጣን ነው ብለው አሰቡ።
14


ያዕቆብ እና ልጆቹ ግራ ተጋቡ። "ገንዘቦቻችንን በስጠን እህል
ውስጥ ተመልሶ አገኘን። እናም ወንድማችን ብንያምን
ማምጣት እንዳለብን ግድ አለን "ብለው ለያዕቆብ
ነገሩት። ያዕቆብ ግን ብንያም እንዲሄድ
አልፈቀደም።
15


ሆኖም ግን ብዙም ሳይቆይ ምግቡ አለቀባቸው።
ስለዚህም ወደ ግብፅ መመለስ ነበረባቸው።
ብንያምም ከእነርሱ ጋር አብሮ ሄደ።
16


ዮሴፍም ብንያምን ባየው ጊዜ አገልጋዮቹን ትልቅ ግብዣ
እንዲያዘጋጁ አዘዛቸው። ወንድሞቹም ተጋብዘው ነበር። "አባታችሁ
ደህና ነው?" ሲል ዮሴፍ ጠየቃቸው። ምናልባትም ሁሉንም
ቤተሰብ እንዴት ሊያመጣ እንደሚችል እያሰበ ሊሆን ይችላል።
17


ዮሴፍ ወንድሞቹ ከብዙ አመታት
በፊት በሠሩት ኃጢአት በ በእውነት
አዝነው እንደሆነ ለማወቅ ፈልጓል።
ከግብዣው በኋላ ዮሴፍ
ወንድሞቹን በስርቆት
ወንጀል ከሰሳቸው።
ዮሴፍም "እናንተን
ለመቅጣት ብንያምን
እንደ ባሪያ አድርጌ
ወስደዋለሁ" አላቸው።
18


ይሁዳም "ጌታዬ ሆይ, በእሱ
ፈንታ ነፍሴን ውሰድ" ብሎ
ለመነው። ዮሴፍም እሱን
ለመሸጥ ሐሳብ አቅርቦ
የነበረው ይሁዳ በእውነትም
እንደተለወጠ አየ።
19


ዮሴፍም ከዚህ በላይ
ለቤተሰቡ ያለውን ፍቅር
መደበቅ አልቻለም። ስለዚህም
በቤት ውስጥ የነበሩት
ግብፃውያን በሙሉ
አስወጥቶ ማልቀስ
ጀመረ።
20













እግዚአብሔር ባሪያውን ዮሴፍን አክብሮታል

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ኦሪት ዘፍጥረት 39-45

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

ክፉ ነገሮችን እንዳደረግን እግዚአብሔር ያውቃል፣
ኃጢአት ብሎም ይጠራዋል።

እግዚአብሔር እጅግ በጣም ስለወደደን አንድያ ልጁን ለመስቀል ሞት አሣልፎ በመስጠት የኃጢአትን ዋጋ በሞቱ ከፍሎልናል። ኢየሱስ ህያው ሆኖ ከሞት መነሣት ወደ ሠማይ አርጓል። አሁን እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይቅር ይለዋል።

ከኃጢአታችሁ ለመመለስ ከወሰናችሁ ለእግዚአብሔር እንዲህ በሉት። እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኔ ኃጢአት ሲል እንደሞተና አሁን ህያው ሆኖ እንዳለ አምናለሁ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባና ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር በል ስለዚህ አዲስ ህይወት ይኖረኛል ደግሞ ከአንተ ጋር ለዘላለም እኖራለሁ። ጌታ ሆይ እንደ ልጅ ለአንተ እንድኖርልህ እርዳኝ አሜን። ዮሐ. 3.16